# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት

# The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church Diocese of Northern California, Nevada, and Arizona Main Office


ነሐሴ ፳፯ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም

**ወኢንኅድግ ማኅበረነ ዘከመ ይለምዱ ካልአን ዳእሙ ንትገሠጽ እስመ ንሬኢ ዘከመ ትቀርብ ዕለት።**
**በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤**
**ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ። ወደ ዕብራውያን 10 ፥25-፳፭**
**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**

## ከነሐሴ ፳፮ እስከ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም / Sept 1 & 2 2023 በደብረ ሰላም ኢየሱስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኦክላንድ የተካሄደው የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት 3ተኛው ዓመታዊ አጠቃላይ ስብሰባ መግለጫ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰሜን ካሊፎርኒያ ፣ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለሦስተኛ ጊዜ የተካሄደው የሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ ስብሰባ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፣ ቆሞስ መልአከ ስብኃት አባ ኃ/ኢየሱስ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ መጋቤ ጥበባት ቀሲስ ተገኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ፣ በሀገረ ስብከቱ የሰሜን ካሊፎርኒያ ወረዳ ቤ/ክህነት ኃላፊዎች ፣ የመምሪያ ኃሊፊዎች ፣ እንዲሁም በሀገረ ስብከቱ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባዔ እና የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች በተገኙበት ነሐሴ ፳፮ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም በይፋ ተጀምሮ በአጀንዳ በተያዙ እና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ጉባዔው ለሁለት ቀናት ውይይት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ለአጥቢያው አብያተ ክርስትያናት እንዲሁም ለሀገረ ስብከቱ በሚጠቅሙ ጉዳዮች ውሳኔ በማሳለፍ ስብሰባው ነሐሴ ፳፯ ቀን ፳፻፲፭ ዓ/ም ተጠናቋል።

ስብሰባው በብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ መሪነት በደብረ ሰላም ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን በጸሎተ ወንጌል እና በጸሎተ ኪዳን ተጀምሯል፡፡ በመቀጠል የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ የጉባኤውን አላማ እና አጀንዳ አስተዋውቅው ብጹዕ ሊቀ ጳጳስ ጉባኤው በንግግር እንዲጀምሩ ጋብዘዋል፡፡ ብጹዕነታቸውም መሰል ጉባኤዎች ተጠናክረው መከናወን እንዳለባቸው ገልጸው የሀገረ ስብከቱን፣ የአድባራትና በሀገር ውስጥ ያሉ መንፈሳዊና ማሕበራዊ አገልግሎቶች ለማጠናከር እንዲሁም

በቤተክርስቲያን የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በጋራ ተሰባስቦ መመካከሩ ጊዜው የሚጠይቀው ተግባር መሆኑን በማሳሰብ የጉባኤውን መጀመር በይፋ አብሥረዋል፡፡

የሀገረ ስብከቱን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በሀገር ስብከቱ ዋና ጸሐፊ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን፦የሀገረ ስብከቱን አስተዳራዊ፣ ለሁለንተናዊ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስፋትና የካህናት ፣ የወጣቶች አገልግሎት በተመለከተ ተጨባጭ ሁኔታ ዳስሷል፡፡ ጉባኤውም የቀረበውን ሪፖርት ካደመጠ በኋላ ጥያቄዎችና ተጭማሪ አስተያየቶችን አቅርቦ ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲገባ አቅጣጫ አስቀምጧል፡

በመቀጠል በሳን ሉዊስ አቢስፖ ካንቲ ሳን ሚጉዌል አካባቢ ስለተገዛው የኖኅተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅ/ዮኃንስ ወቅድስት አርሴማ ገዳም በብጹእነታቸው አማካይነት አጠቃላይ ገለጻ ተደርጓል። ብጹእነታቸው፡-

- ስለገዳሙ አሁናዊ አገልግሎት እና በጊዜያዊነት በመጡ አገልጋዮች የገዳሙ መንፈሣዊ እና የጽ/ቤቱን አገልግሎት እየተከናወነ እንደሆነ፤
- ገዳሙን በአገልግሎት ለማጠናከር አገልጋይ መነኮሳት እና መነኮሳይቶችን በቅጥር መልክ ከኢትዮጵያ ለማምጣት በሲኖዶስ ደረጃ እንቅስቃሴ የተደረገ ቢሆንም በአሜሪካ የኢሚግሬሽን ህግ መሠረት ቅጥሩን ለመፈጸም ጉዳዩን በቅርበት ክትትል እየተደረገበት ያለ መሆኑን፤
- የገዳሙ ዓላማ፤ በዋናነት ሰውን የማዳን እና የልማት ሥራ እንደሆነ በመሆኑ፣ የገዳሙ ባለቤት የመላውኢትዮጵያውያን ስለሆነ ሀገረ ስብከቱ እና በሀገረ ስብከቱ ሥር ያሉ ካህናት ፣ ምእመናን እና አጥቢያዎች የገዳሙን አገልግሎት ከማስቀጠል እና ከማጠናከር አንጻር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እና ድርሻ እንዲወጡ፤
- አዲሱን የገዳም ቦታ ግዢ ለመፈጸም በኮሜዲያን እሸቱ አማካይነት በተደረገ የቀጥታ ስርጭት የገንዘብ ማሰባሰብ መርሐግብር $4.8 million በመሰብሰብ ገዳሙን ከባንክ ብድር ነጻ የማድረግ ሥራ የተሠራ የተከናወነ መሆኑንና በቅርቡ ከበጎ ፈቃደኛ ግለሰቦች ከተገኘ ዕዳ ሙሉ በሙሉ ነጻ

እንደሚሆን፤ ገልጸው አሁን ያለውን የአገልግሎት ሁኔታ ለማስቀጠል በኢት/ኦ/ተ/ቤ/ የገዳም ሥርዓት ብቻ መቀጠል እንደሚገባው ብጹእነታቸው ማሳሰቢያ ሰጥተዋል።

በመቀጠል “ኅብረታዊ ህልውና እና በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን” በሚል የውይይት መነሻ አሳብ ቀርቦ በእምነት በሥርዓተ አምልኮና በአስተዳደር ረገድ አንድነታችን የሚጠናከርበት መነሻ አሳብ ተዳስሶ ጉባኤው ውይይት አድርጎበታል፡፡ **ጉባኤውም**

- በሥርዓተ አምልኮ እና አስተዳደራዊ ወጥነት አተኩሮ ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን በጥናት እየሠራ መሆኑን እና ውሣኔው እስኪመጣ አጥቢያዎች በመግባባት እና በመተሳሰብ መንፈሣዊ አገልግሎቱን እና አስተዳደሩን አጣጥመው እንዲያካሂዱ፤
- ቤተ ክርስቲያን አሁን ካለባት ውስጣዊ እና ውጫዊ ፈተና አንጻር ከምንጊዜውም በበለጠ አገልጋዮች እርስ በርስ በመደጋገፍ እና በመተሳሰብ ወደ ሰላም እና መተባበር እና የአንድነት አገልግሎት ቀጣይነት ያለው ተግባር እንዲኖር፤
- በተጨማሪም የአገልግሎት ወጥነትን ለማስቀጠል ፣ የገዳሙን የአብነት ት/ት መርሐግብር ለመቅረጽ እና ለማስቀጠል እንዲሁም የቤ/ክርስቲያን ሥርዐተ አምልኮ መመሪያዎችን እና የቅዳሴ መከታተያ ሁፎችን በቤ/ክርስቲያን ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ጽሁፍ በሀገረ ስብከቱ ዌብሳይት በተቀናጀ መልኩ እንዲኖር ጉባዔው ሁለት ኮሚቴዎችን የሰየመ ሲሆን ለአፈጻጸሙም የኮሚቴው አባላት የድርሻቸውን በትጋት እንዲፈጽሙ በብጹእነታቸው መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

በመቀጠል የወጣቶች እና ሕጻናት አያያዝ ልምድ ልውውጥ በተመለከተ ጉባኤው የየአጥቢያውን ልምድ ያደመጠ ሲሆን፤ በአገልግሎቱ የገጠመውን ችግር፣ በጎ ጎንና በጎ ዕድል አጢኖ ቋንቋን መሠረት ባደረገ መልኩ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት በሀገራዊ ትምህርትም ታቅፎ በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሰጥ አቅጣጫ ሰጥቷል፡፡

በሁለተኛው ቀን የጉባኤው ውሎ "**ቤ/ክርስቲያን ትናንት እና ዛሬ** በሚል ርእስ በሀገረ ስብከቱ የካህናት አገልግሎት መምሪያ አማካይነት ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን፤ ቤተ ክርስቲያን የነበራትን ታሪካዊ ሥፍራ፣ የገጠማትን ፈተናዎች፣ በሰሜን አሜሪካ ያሳካችውን ስኬትና ችግሮች እንዲሁም አሁን ድረስ የሚስተዋሉ የሰላም እጦቶች መፍትሔ የሚያገኝበትን መንገድ አቅርቦ ጉባኤው በጥልቀት ተወያየቶበት መፍትሔ የሚገኝበትን አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ሀገረ ስብከቱን፣ በሀገረ ስብከቱ ሥር የሚገኙ አድባራት ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከርን በተመለከተ እና በልዩ ልዩ አጀንዳ በቀረበ ኃሳብ ጉባኤው ሰፊ ውይይት በማድረግ፡-

- ሀገረ ስብከቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማጠናከር ከየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ በየወሩ ፈሰስ እንዲደረግ ከዚህ ቀደም በተወሰነው መሠረት ተፈጻሚነቱ እንዲጠናከር
- አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት መዋቅርን በጠበቀ መልኩ እንዲያደርጉ
- የአገልጋዮችን የህግ ደህንነት የመጠበቅ እና እንደ አስፈላጊነቱም የተጠናከረ የህግ ሥራ የሚሰራበትን ጉዳይ ጉባዔው በሠፊው የመከረ ሲሆን ጉዳዩ በሀገረ ስብከቱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንዲታይ እና ተቋማዊ የተጠናከረ ሥራ እንዲሠራ
- በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ያለው አገልግሎት ወጥነት ያለው እንዲሆን በጋራ ስምምነት አድርጎ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል፤

1. በሳን ሉዊስ አቢስፖ ካውንቲ ሳን ሚጉዌል አካባቢ የተገዛው የጥንተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅ/ዮኃንስ ወቅድስት አርሴማ ገዳም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ በሰሜን አሜሪካ ለምታደርገው መንፈሳዊ አገልግሎት በምልክትነት የሚታይ በመሆኑ ይህንን ራእይ ተግባራዊ እንዲሆን ፊት በመቅደም ዋናውን ድርሻ ለተወጡት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር ጉባኤው በልጅነት መንፈስ ዕውቅና እንሰጣለን

2. የኖኅተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅ/ዮኃንስ ወቅድስት አርሴማ ገዳም የሚሰጠውን መንፈሳዊና ማሕበራዊ አገልግሎት ለማጠናከር፣ እንዲሁም ቀሪ ዕዳውን ክፍሎ ለመጨረስ አስፈላጊውን ተግባር ለማከናወን ቃል እንገባለን፡፡
3. የህጻናትና የታዳጊዎች አያያዝና አገልግሎት በሁሉም አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ዋና የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ እንዲሠራ ስምምነት አድርገናል፤ ለተግባራዊነቱም ተግተን እንሠራለን፡፡
4. በሀገረ ስብከቱ የሚከናወኑ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት ወጥነትንና የአንድነት መንፈስን የሚያጎለብት እንዲሆን ከፊት ቀዳሚ በመሆን እንሠራለን፡፡
5. በሀገረ ስብክቱና በአጥቢያዎች መካከል ሊኖር ስለሚገባው መዋቅራዊና ሰላማዊ ግንኙነት ከምንጊዜውም በበለጠ ለመሥራት ቃል እንገባለን፡፡
6. ለ ፳፻፲፮ የጥቅምት ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ከሀገረ ስብከታችን የሚጠበቀውን የጠቅላይ ቤ/ክህነት ዓመታዊ ፈሠስ በተሻለ የገንዘብ መጠን ለማሳደግ ሀገረ ስብከቱ የሚያቀርበውን የገንዘብ አስተዋጽዖ መጠይቅ ለማስተናገድና ለመፈጸም ቃል እንገባለን፡፡

በመጨረሻም ይህን ጉባዔ የተሳካ ለማድረግ የተባበሩ በሰሜን ካሊፎርኒያ ወረዳ ቤ/ክህነት ውስጥ ያሉ ሦሥቱ አድባራት ማለትም ደብረ ሰላም ኢየሱስ በኦክላንድ ፣ ደብረ ሰላም ቅ/ሚካኤል በኦክላንድ እና ደብረ ይድራስ ቅ/ጊዮርጊስ በሳን ፍራንሲስኮ ፣ የአጥቢያው አስተዳዳሪዎች ፣ ምእመናን እና መዘምራን ፣ ጥናታዊ ጽሁፎቹን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማዘጋጀት ላቀረቡ አካላት ፣ እንዲሁም በጉባዔው ለመሳተፍ ከሩቅም ከቅርብም ለመጡ የሀገረ ስብከቱ የመምሪያ ኃላፊዎችና የወረዳ ቤ/ክህነት ኃላፊዎች ፣ የሰበካ ጉባዔ ተወካዮች እና የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ዶ/ር ምሥጋና አቅርበዋል። ለተሰጡ መመሪያዎችና ለተላለፉ ውሳኔዎች እንዲሁም ለተገለጸው የጋራ መግለጫ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ በማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ቆሞስ መልአከ ስብሃት አባ ኃ/ኢየሱስ የተጠናከረ መመሪያ ያስተላለፉ ሲሆን የ ፳፻፲፮ ዓ/ምየሀገረ ስብከቱ ዓመታዊ አጠቃላይ ስብሰባ በሣክራሜንቶ ከተማ እንዲሆን ጉባዔው በመወሠን በብጹእነታቸው ጸሎትና ቡራኬ ስብሰባው ተጠናቋል።